የሕዳር **2020** ዓ.ም ጠቅላላ ምርጫ ለኪንግ ካውንቲ መራጮች ለወሰኝ የካፒታል ኢንቨስትመንቶች የካፒታል ኢንቨስትመንት ቦንድ
እርምጃን በማፅደቅ ለሀርበርቪው የህክምና ማዕከል /**Harborview Medical Center** ድጋፍ የሚሰጡበት እድል ይፈጥርላቸዋል
የ20 አመቱ ቦንድ የሚፀድቅ ከሆነ የወሳኝ የጤና እንክብካቤ አቅም ግንባታን፣ የዘመናዊ የኢንፌክሽን ቁጥጥር ደረጃዎችን ማሻሻልና
ማስፋፋትን፣ እና የባህሪ ጤና ፍላጎቶች አቅምን ማስፋፋትን ጨምሮ ለሀርበርቪው የጤናና ደህንነት ማሻሻያዎችን ያመጣል።
ይህ ቦንድ አሁን ያለውን የአእምሮ ጤናና የባህሪ ጤና ትምህርትን፣ ስልጠናና አገልግሎቶችን የፈውስ መቼት የተቀናጀ ወደሚሆንበት
የተሟሉ ቀጣይነት ያላቸው የባህሪ ጤና አገልግሎቶች ወሚቀርቡበት ሰፊ የአገልግሎት መስጫነት ያሳድጋቸዋል። እነዚህ
ኢንቨስትመንቶች አገልግሎቶቻቸውን የሚሰጡት ለተጋላጭ ማህበረሰቦች ብቻም ሳይሆን ከቀውስ ማጋጠም በፊት ህክምና ለሚያገኙ
ለሁሉም ግለሰቦች አገልግሎት በመስጠት የሀብት ቁጠባ ከማምጣት ጎን ለጎን አኗኗርን ይቀይራሉ።
የሀርበርቪው የባህሪ ጤና ተመላላሽ ታካሚዎች ክሊኒኮች የታካሚ መኝታ ክፍሎቻቸው ከመሙላታቸውም በተጨማሪ የባህሪ ጤና
አገልግሎቶች መስፋፋት አስፈላጊነት ማስረጃን ከየቦታው ማየት ይቻላል።
የቦንድ መርሀግብርን የሚይዙት ምክረ ሀሳቦች ከህክምና ኤክስፐርቶች፣ የወሊድ፣ የባህሪ ጤና ኤክስፐርቶች፣ የመኖሪያ ቤት እና መኖሪያ
ቤት አልባ ማህበረሰቦች እና ሌሎች የተወሰዱ ግብአቶችን ጨምሮ የሀርበርቪው እና የሰፊው የኪንግ ካውንቲ ማህበረሰብን የካፒታል
ፍላጎቶች ለመረዳትና ለይቶ ለማወቅ የተዘጋጀ ለሁለት አመታት ያክል የተካሄደ የባለድርሻ አካላት አሰራርን ተከትለው የተሰጡ ናቸው።
ይህ ቦንድ አሁን ያለውን የገንዘብ ተጣይ ከመተካቱም በተጨማሪ $600,000 ዋጋ የሚከፍሉ መካከለኛ የኪንግ ካውንቲ አባወራዎች ላይ
በየአመቱ $61 ተጨማሪ ክፍያ ያስከትላል። በአመታዊ ተጣይ መጠን ላይ የተገመተውን ለውጥ ለማየት እዚህ ጋር ይጫኑ።
የሚወሰዱ እርምጃዎች ጥቅል ማብራሪያዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:
• በአስቸኳይ ጊዜ፣ በአደጋ ጊዜ፣ ወይም በወረርሽኝ መከሰት ወቅት የሆስፒታሉን ተጨማሪ ታካሚዎች የመገልገል አቅም
ለማሳደግ እና ዘመናዊ የኢንፌክሽ ቁጥጥር እና የግላዊነት ደረጃዎችን እንዲያሟላ ለማስቻል የሚካሄድ የአዲስ የህክምና ህንጻ
ግንባታና አሁን ያለው ቦታ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ፤
• የድንገተኛ ህክምና መምሪያ ማስፋፊያ፤
• እያደገ የመጣውን የባህሪ ጤና ፍላጎት ለማሟላት የሚካሄድ የአዲስ የባህሪ ጤና አገልግሎቶች መስጫ ህንጻ ግንባታ፤ እና
• የታካሚዎች፣ ሰራተኞችና ጎብኚዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ በጠቅላላ የሀርበርቪው ካምፓስ ላይ የሚካሄዱ የርዕደ መሬት
መቋቋሚያ ማሻሻያዎች።